# ስድስተኛ ትምህርት

ከጥር 27 — የካቲት 3 Feb 4-10/2017

## መንፈስ ቅዱስና የተቀደሰ ሕይወት መኖር

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፦ 1ጴጥ. 1:14-16፣ ኢሳ. 6:3፣ ዕብ. 12:14፣ 1ቆሮ. 6:11፣ 1ጢሞቴ. 1:8፣ መዝ. 15:1-2።

> **የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፦ "የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ፤ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ነቀፋ ይጠበቁ።" (1ተሰ. 5:23)።**

ለአምላካዊው ቅድስና ምላሽ የማይሰጥ ስብዕና ይዞ--እግዚአብሔር ኃጢአትንና ክፉን እንደሚጠላ በተገለጸው ሃሳብ ላይ እምብዛም ትኩረት አለመስጠት ቀላል ነው። ቅድስና በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ መሰረታዊ ርዕስ ጉዳይ ነው። እንደ የሱስ ያለ አፍቃሪና ንጹህ ስብዕናን በመያዝ ቅድስናን እንደጠበቁ መዝለቅ እያንዳንዱ ክርስቲያን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። አንዳንዶች ሊያሳዩ የሚሞክሩት እ ኔ ካ ን ተ / ካ ን ቺ በ ተ ሻ ለ ቅ ዱ ስ ነ ኝ የሚል አንደምታ ያለው አባባል ድንጋጤ ሊፈጥርብን ቢችልም ነገር ግን ቅድስናን እንደ ጠበቁ የመዝለቁንና የተቀደሰ ህይወት የመምራቱን አንደምታ እንደ ዘበት ከአእምሮአን ስናወጣው እንስተዋላለን።

የእግዚአብሔር ፍቅርና ቅድስና እንደ ማይለያዩ ሆነው በአንድ ተሳስረዋል። የእግዚአብሔር ፍቅር ቅድስና ከሌለው ፍቅሩ ብቻውን--አብልጦ ወደ ስሜት ያዘነበለና ቡቡ የመሆን አደጋ የተጋረጠበት ይሆናል። አምላካዊ ፍቅር የሌለበት ቅድስና ብቻውን ደግሞ ጥብቅ፣ ሊቀርቡት የማይችሉት ዓይነትና ቀዝቃዛ ይሆናል። ስለዚህ ሁለቱም ባህሪያት ማለትም ፍቅሩና ቅድስናው ለአምላካዊው ተፈጥሮ እጅግ ወሳኝና መሰረታዊ ነገሮች ናቸው።

መንፈስ ቅዱስ ቀጣይነት ካለው ቅድስናችን ጋር ሊስተዋል በማይችል መስመር ተገናኝቶአል። ደግሞስ መ ን ፈ ስ ቅ ዱ ስ ስሙ---መጠሪያው ደግሞ "የቅድስና መንፈስ" (ሮሜ. 1:4) አይደል? ስሙ የእግዚአብሔርን ቅድስና እንደሚያስታውሰን ሁሉ ኃጢአተኞች የራሱን ቅድስና መልክ እንዲይዙ ማድረግ ታላቁ አምላካዊ ምኞት ነው።

በዚህ ሳምንት ጥናታችን ቅድስናና የተቀደሰ ህይወት መኖር ምን ማለት እንደሆነ በቅርብ ለመመልከት እንሞክራለን።

*እሁድ ጥር 28* *Feb 5*

### የእግዚአብሔር ቅድስና

ጥቅሶቹን ያንብቡ፦--1ጴጥ. 1:14-16። የቅድስና የመጨረሻው ግብ ራሱ እግዚአብሔር የሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ የሆነው ለምንድን ነው? የተቀደሰ ህይወት እንዲኖሩ አነሳሽ ምክንያት የሆነዎ ነገር ምንድን ነው? እግዚአብሔር ቅዱስ ነው የሚለው አነጋገር ፍቺ ምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የእግዚአብሔርን ቅድስና ቸል ብሎ ለፍቅሩ ብቻ አጽንኦት መስጠት በብዙዎች የተለመደ አካሄድ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑ እሙን ቢሆንም ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የቀረበው የቅድስናው ጽንሰ ሃሳብ ከማንኛውም ባህሪው በላቀ ከእግዚአብሔር ስም ጋር የተሳሰረ ነው (መዝ. 89፡18፣ ኢሳ. 40:25፣ ኤር. 51:5፣ ሕዝ. 39:7፣ ራእ. 4:8)። ቅድስና የአምላካዊውን ተፈጥሮ ንጽንናና ግብረገባዊ ፍጽምና ይገልጻል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ስንል ፍጹም መልካምና ፍጹም ክፋት የማያውቅ አምላክ ነው--እንደ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቅድስና የሁሉም ባህሪያቱ ፍጽምና ማሳያ ነው።

እግዚአብሔር ፍጹም ኃያል፣ ፍጹም አዋቂና በሁሉም ስፍራ የሚገኝ አምላክ ሆኖ-ፍጹም የሆነ ቅድስና ግን ከሌለው እንዲህ ያለው አምላክ የምንወደው ሊሆን ሲገባ በተቃራኒው እጅግ የሚያሸብረንና የሚያስፈራን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው።

የእግዚአብሔር ኃይል ቅዱስ ነው። አምላካዊ ምህረቱ ቅዱስ ነው። አዋቂነቱ ቅዱስ፣ ፍቅሩም እንዲሁ ቅዱስ ነው። ነገሩን ከዚህ አኳያ ስንመለከተው ቅድስና ከመለኮታዊው ማንነት ጋር መነጣጠል የማይችልና ከተፈጥሮው ጋር በአንድ የተሳሰረ ቃል ነው። የእግዚአብሔርን የተቀደሰና ንጹህ ማንነት መካድ ምናልባትም አምላካዊውን ሕልውት ከመካድ በላይ የከፋ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ስንል ሙሉ ለሙሉ ከኃጢአት የተነጠለና እርሱ በራሱ የሚወክለውን በጎ አጥብቆ የሚሻ እንደማለት ነው። በሌላ አነጋገር ቅድስና ለግንኙነትና ለግብረገብ የሚሰጥን ዋጋ ያመለክታል። ይህ ደግሞ ከኃጢአት መለየትንና በአምላካዊው ክብር ዙሪያ የሚደረግን አምልኮ በአንድ አጠቃሎ ይዞአል።

በኢሳ. 6:3 እና በራእ. 4:8 እግዚአብሔር "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ" በሚሉ ቃላት ተገልጦ እንመለከታለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ትኩረታችንን ወደ ተፈለገው ሃሳብ ለመሳብ ሲሹ፤ በእጅጉ አስፈላጊ ላሉት ክፍል የተለየ አጽንኦት በመስጠት ያንን ቃል ደጋግመው ይጽፋሉ። የሱስ አስፈላጊ ያላቸውን ቃላት በመደጋገም ትኩረታችንን ሲስብ ይታያል "እውነት፣ እውነት" (ዮሐ. 5:24፣ 6:47፣ ወዘተ.) ወይም "ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም" (ማቴ. 23:37)። ወይም ስምን ደጋግሞ በመጥራት "ማርታ፣ ማርታ" (ሉቃስ 10:41)። የሱስ ከተናገራቸው ከእነዚህ ቃላት በተለየ ሶስት ጊዜ የተጠቀሰው የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚያሳየው ቃል ብቻ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ቃሉ በተለይ ከፍ ያለ አጽንኦት የሚሰጠው መሆኑን ያሳያል። አምላካዊው ተፈጥሮ በእርግጥም ቅዱስ ነው። እርሱ ንጹህና መልካም ነው።

ኃያሉ አምላካችንና ፈጣሪያችን ቅዱስና አፍቃሪ ባይሆን--ምን ያህል በፍርሐት የተዋጡ ሊሆኑ ይችሉ ነበር? እግዚአብሔር ያው እግዚአብሔር ሰለሆነ ምን ያህል አመስጋኞች ልንሆን እንደሚገባ መልስዎ ምን ይነግሮታል?

*ሰኞ ጥር 29* *Feb 6*

## የቅድስና ተፈጥሯዊ ባህሪ

"ወደ የሱስ በቀረቡ ቁጥር ስብዕናዎ ይበልጥ በእንከን እንደተሞላ መመልከት ይጀምራሉ። ከቀድሞው ይልቅ የአሁኑ እይታዎ በተሻለ እየጠራ ስለመጣ የእርስዎን ፍጽምና የጎደለው ማንነት ከእርሱ ፍጹም ተፈጥሮ ጋር በስፋትም ሆነ በጥልቀት ማነጻጸር ይጀምራሉ። ይህ ደግሞ በእርስዎ ውስጥ ይሰለጥን የነበረው የሰይጣን ማሳቻ ዘዴ እየከሰመ፤ ለስብእናዎ ሕይወት የሚሰጠው የእግዚአብሔር መንፈስ

በውስጥዎ እያንሰራራ መሆኑን አመላካች ነው፡፡”–Ellen G. White, S t e p s t o Christ, pp. 64, 65.

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ኤፌ. 1፡4፣ 5፡25-27፣ ዕብ. 1214፡፡ ለሕዝቡም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን--የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ቅድስና የእግዚአብሔር ስጦታና ትእዛዝ እንደመሆኑ ይህን ቅድስና ለማግኘት ልንጸልይና በየቀኑ ለሌሎች ገልጠን ማሳየት በሚያስችለን መልኩ አጥብቀን ልንሻው ይገባል፡፡ ቅድስና በየቀኑ ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን ጉዞ ተገልጦ መታየት የሚችል የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡16፣ 22፣25)፡፡ ቅድስና ክ ር ስ ቶ ስ ን መ ም ሰ ል የሚል ትርጉም አለው፡፡ ትርጉሙ--የየሱስ መሆን፣ ልክ እንደ ልጁ ትእዛዛቱን በፍቅር እየታዘዙ ይበልጥ እርሱን ወደ መምሰል ደረጃ መሸጋገር የሚል አንደምታ አለው፡፡ ለአምላካዊው አገልግሎት መለየት --ከቅድስና ጽንሰ ሃሳብ ጋር ተጓዳኝነት ያለው መሰረታዊ ፍቺ ነው፡፡ በሌላ በኩል ቅድስና--በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅና ንጹህ ሊያስብል የሚችል በግብረገብ የታነጸና ምርጥ መንፈሳዊነትን የያዘ የሚል አንደምታ አለው፡፡ እነዚህ ሁለቱም ገጽታዎች መነጣጠል አይኖርባቸውም፡፡

በአዲስ ኪዳን አማኞች ከየሱስ ጋር በዓይነቱ ልዩ የነበረ ግንኙነታቸውንና ለተለየ አገልግሎት መጠራታቸውን ተከትሎ ቅዱሳን ተብለው ተጠርተዋል፡፡ የእነዚህ ሰዎች ቅዱሳን ተብሎ መጠራት ከግብረገብ አኳያ ፍጹማን ወይም ኃጢአተኞች ያልሆኑ የሚል ስብዕና ኖሯቸው ሳይሆን--ነገር ግን ንጹሁንና ቅዱሱን ሕይወት በተለወጠ ሕይወት መኖር በመጀመራቸው ነው (ይህን ሃሳብ ከ1ቆሮ. 1፡2 ጋር ያስተያዩ፡፡ በጥቅሱ የቆሮንቶስ ሰዎች ኃጢአት የማያውቁ ወይም ፍጹማን ባይሆኑም ነገር ግን ጳውሎስ ቅዱስ ወይም ቅዱሳን በማለት ይጠራቸዋል)፡፡ ያለ ቅድስና ጌታን ማየት የማይቻል እንደመሆኑ አማኞች በየቀኑ በቅድስና ሕይወት እንዲመላለሱ ይገሰጻሉ (ዕብ. 12፡14)፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱን አማኝ የሚቀበልበት መንገድ ገና ከጅምሩ ፍጹም ነው፡፡ የእኛ የፍጽምና ጉዞ ግን የዕድሜ ልክ ሂደት እንደ መሆኑ ከትናንት ይልቅ ዛሬ በተሻለ ቅድስና ላይ ለመገኘት ጥረት እያደረግን ወደ አዳነን እንከን ዐልባ አምላካዊ አምሳል ይበልጥ እየተለወጥን እንሂድ፡፡

ቅዱስ በመሆንና በቅድስና ሕይወት በመቀጠል መካከል አሳሳቢ የሚመስል ነጥብ አለ፡፡ ስለ እኛ መሥዋዕት የሆነውን የሱስ የግል አዳኛችን አድርገን አንዴ ከተቀበልንና የእግዚአብሔር ንብረት መሆናችንን ከተገነዘብን በኋላ በቅድስና ሕይወት መቀጠል ተለይቶ የሚታየው እንዴት ነው?

ማክሰኞ ጥር 30 *Feb 7*

## የቅድስና መንስኤ

የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ቅድስና ምን ይሉናል፡--1ቆሮ. 6፡11፣ ቲቶ 3፡5፣ ዕብ. 13፡12?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ቅድስናችን ገቢራዊ መሆን የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል (2ተሰ. 2፡13፣ 1ጴጥ. 1፡2) ይኸውም በእምነት ነው (ዕብ. 11፡6)፡፡ “አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል” (1ቆሮ. 6፡11)፡፡ የሱስ በቅድስና ዕድሜያችንን ሙሉ የምናድግበትን መንገድ በመቀየስ የመንፈስ ፍሬ በእኛ ውስጥ እንዲታይ ያደርጋል፡፡ “የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው” (2ቆሮ. 3፡18)፡፡

ጳውሎስ በገላ. 5፡16-17 ምን እያለን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ በዚህ ጊዜ ፍጻሜ ያገኛል የማይባል መጨረሻ የሌለው ውጊያ ይካሄዳል፡፡ ኃጢአት በእኛ ውስጥ ማደሩ ይህ የምንጋፈጠው የማያባራ ፍጥጫ በውጥረት የተሞላ ገጽታ እንዲይዝ አድርጎታል (ሮሜ 7፡20)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ዕድሜ ዘመኑ መጨረሻ ላይ የሚከተለውን ሲናገር በእርግጥም ስለዚህ ውጊያ ጠንቅቆ ተረድቶ ነበር "ወንድሞች ሆይ፤ እኔ ገና እንደያዝሁት አድርጌ ራሴን አልቆጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፤ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ፡፡" (ፊልጵ. 3፡13, 14)፡፡

በዕብ. 12፡1-2 እንደ ቀረበው በኃጢአት ላይ የምናውጀው የእምነት ዘመቻ ምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

"የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት" (ዕብ. 12፡2) በሚል መርኅ የውጊያው ተካፋዮች እንድንሆን ተጠርተናል፡፡ ከኃይማኖተኝነታችን ጋር ቁርኝት ባላቸው ነገሮች አብልጠን ራሳችንን ስናስቀድም እንስተዋላለን፡፡ ዐይኖቻችንን በብቸኝነት በኃጢአት ላይ ድል ሊሰጠን በሚችለው እግዚአብሔር ላይ በማሳረፍ ፋንታ--ትኩረታችን ባገኘነው ድልና በደረሰብን ውድቀት ላይ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ የሱስ እንድንመለከት ሲረዳን--ኃጢአት የመሥራት ምኞታችን ስለሚከስም በቀላሉ ያደናብረን የነበረ ማንኛውም ነገር ከፊታችን ገሸሽ ይላል (ዕብ. 12፡1)፡፡ ነገር ግን ትኩረታችንን በኃጢአታችንና በጉድለቶቻችን ላይ ስናደርግ ወደ የሱስ ሳይሆን ወደ ራሳችን መመልከት እንጀምራለን፡፡ ለውድቀት የዳረጉንን ነገሮች ስንይዛቸው በቀላሉ ተስፋ እንድንቆርጥ በማድረግ ወደ ሽንፈት ይመሩናል፡፡ ነገር ግን የሱስን መያዝ ስንችል መበረታታት በማግኘት ባለ ድል ሕይወት መኖር እንችላለን፡፡

አንድ ሰው "በመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋ የተሰጠውን በኃጢአት ላይ ድል ማግኘት የምችለው እንዴ ነው?" ብሎ ቢጠይቆት መልስዎ ምን ሊሆን ይችላል? ለምን? መልስዎን በሰንበት ትምህርት ጥናት ላይ ይዘው ለመምጣት ይሞክሩ፡፡

*ረቡዕ የካቲት 1* *Feb 8*

## የቅድስና ሕጉና ደንቡ--ትእዛዛቱ ናቸው

እግዚአብሔር ትእዛዛቱን እንድንጠብቅ ጥሪ እንዳደረገልን እናውቃለን፡፡ ትእዛዛቱን በመጠበቃችን የማንድን እስከሆንን ድረስ የመጠበቁ አስፈላጊነት ምኑ ላይ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የቅድስና ጽንሰ ሃሳብ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ይሰጠናል፡፡

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ሮሜ. 7፡12፣ 1ጢሞቴ. 1፡8፡፡ ጳውሎስ ሕጉን ለመግለጽ ምን ዓይነት ባህሪያትን ይጠቀማል? ሕጉ የእግዚአብሔርን ጸባይ እንዴት ያንጸባርቃል?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ሕጉ ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው፡፡ እነዚህ ሶስት ባህሪያት በትክክል የሚገልጹት እግዚአብሔርን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ሕጉ የእግዚአብሔር ጸባይ መገለጫ ነው፡፡

በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ሕይወት መኖር ማለት በእግዚአብሔር ሕግ ላይ በተጻፈው መሰረት መመላለስ ነው። የቅድስናው ሕግ መለወጥ የማይችል ነው።

በትእዛዛቱ የተንጸባረቁትም ሕጎች በማንም የማይለወጡ ናቸው። ሕጉ አለመሻሩን-ይልቁንም እያንዳንዱ የሕጉ ክፍል ተፈጻሚነት ሊያገኝ እንደሚገባ የሱስ አጽንኦት ሰጥቶ ተናግሮአል (ማቴ. 5:17-19)። ሕጉን መጠበቅ የታማኝነት መግለጫ እንጂ-ሕጋውያን ወይም ሕግን ጠብቀው ለመዳን የሚሞክሩ ሊያስብል አይችልም። የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቃችን ሊያድነን አይችልም--ፈጽሞ አያድነንም። ሕጉ ወይም አስርቱ ትእዛዛት የደኅንነት መንገድ ሆነውን አያውቁም--የዳኑት የሚጓዙበት መንገድ እንጂ። ሕጉ የፍቅር ጉዞአችንን የምናደርግበት መጫሚያችን ሆኖ ራሱን መግለጹን ተከትሎ የሱስ--"ክፋት ስለሚገን የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል" (ማቴ. 24:12) በማለት የተናገረበት ምክንያቱ ይኸው ነው--ሕጉ ሊሰጠው የሚገባ ዋጋ በቀነሰ ቁጥር ፍቅር እየደበዘዘ ይሄዳል።

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ሮሜ 13:10፣ ማቴ. 22:37-40። ፍቅር የሕግ ፍጻሜ የሆነው ለምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የቅድስና ሕግና ደንብ መሰረቱ የእግዚአብሔር ሕግ ሲሆን፤ የቅድስና እምብርት ደግሞ ፍቅር ነው። ፍቅር--እግዚአብሔር ለሠራልን የደኅንነት ሥራ ምላሽ የምንሰጥበት መንገድ እንደ መሆኑ፤ ይህ ፍቅር ለእርሱ በምናሳየው ታማኝነት ይገለጻል። ለእግዚአብሔር ሕግ ተገቢውን ትኩረት የማንሰጥ--አፍቃሪ ትእዛዛቱን የምንጠብቅ ልጆቹ ሳንሆን የየሱስ መልካም ደቀ መዝሙር መሆን የምንችለው እንዴት ነው? በልብ ውስጥ ምንም ፍቅር ሳይኖር በሕጉ ላይ የተቀመጡትን ቃላት መጠበቅ የሚቻል ቢሆንም፤ ትእዛዛቱን ሳይጠብቁ እውነተኛውን ፍቅር መግለጽ ግን አይቻልም። እውነተኛ ፍቅር ታማኝ በመሆን ምኞት የተሞላ ነው። ፍቅር ሕጉን አይሰርዝም--ያጸናዋል እንጂ!

ሕጉ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር መግለጫ የሆነው ለምንድን ነው? ፍቅርና መታዘዝ የሚዛመዱት እንዴት ነው?

*ሐሙስ የካቲት 2* *Feb 9*

## ቅድስናን ያለማቋረጥ ጠብቆ መንዝ

የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ቅድስና ምን ይነግሩናል? መዝ. 15:1-2፣ ኤፌ. 4:22-24፣ 2ጢሞቴ. 2:21።

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ፈጥረን ሐሴት ለማድረግ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት የምንመሰርትበት ቅድመ ሁኔታም ነው። ጸባያችን እስከ መጨረሻው አብሮን የሚዘልቅ እንደ መሆኑ ወደ ሰማይ ይዘነው ልንሄድ የምንችለው ብቸኛው ነገር ነው።

አዳዲስ ልማዶችንና ጸባዮችን ማጎልበት ብንችልም ነገር ግን በራሳችን ጥረት ራሳችንን መቀደስ አንችልም። ወደ ቅድስና የሚመራን መንፈስ አዲስ የሆነውን ልማድ ማጎልበት እንድንችል ይረዳናል። በተለይ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ምግባር ጋር ቁርኝት ያላቸው የሚከተሉት ዓይነት ልማዶች ለክርስትና ጉዞአችን በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው። ትዕግሥት፣ ፍቅር፣ ታማኝነት፣ ደግነት፣ መልካምነት፣ ጨዋነትና ራስን መግዛት።

ልባችን በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ መልካም የሆነውን ለማድረግ መነሳሳት እንደምናገኝ ጥርጥር የለውም፡፡ ሆኖም የሚቀድሰንና በእኛ ውስጥ የጀመረውን ሥራ የሚጨርሰው እግዚአብሔር መሆኑን አብልጠን እንዘነጋለን (ፊልጵ. 1፡6)፡፡ አንዳንዴ በቂ የጸሎት ጊዜ ወስደን ከእርሱ ጋር ሐሴት ልናደርግባቸው የሚገቡንን ሰዓታት በሌሎች ለእርሱ በምንሠራቸው የተለያዩ ሥራዎች እናጣብባቸዋለን፡፡ እጅግ በሥራ ከመጨናነቃችን የተነሳ ለጸሎት የሚሆን ጊዜ የምናጣ ከሆነ በእርግጥ ክርስቲያን ለመሆንም በቂ ጊዜ አይኖረንም፡፡

ምናልባት ዕውቀታችንና ስኬታችን በራሳችን እንድንመካና እንድንተማመን ስላደረገን፤ ችሎታችንን ተጠቅመን በጥንቃቄ ያዘጋጀናቸውን መርኀ ግብሮች እናካሂዳለን፡፡ በዚህም ያለ መንፈስ ቅዱስ--ከክርስቶስ በተነጠለ አካሄድ የምንሠራው ሥራ አንዳችም ውጤት ሊያስገኝልን እንደማይችል እንዘነጋለን፡፡

በልዩ ልዩ መንፈሳዊ መርኀ ግብሮች ላይ በንቃት ተሳታፊ መሆን ቅድስና አይደለም፡፡ ምናልባት አንዳንዶች ለጌታ ታላላቅ ሥራዎችን እንደሠሩ ሆኖ ሊሰማቸው ቢችልም ነገር ግን በትክክል እርሱን እየተከተሉ ላይሆኑ ይችላሉ "በዚያ ቀን ብዙዎች 'ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?' ይሉኛል፡፡ በዚያ ጊዜ 'ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ!' ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ፡፡" (ማቴ. 7፡22-23)፡፡ በእግዚአብሔር በመጠራትና ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለመሥራት በመገፋፋት መሃል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ በመጀመሪያ በቂ ጊዜ ወስደን የእግዚአብሔርን የጥሪ ድምጽ ካልሰማን በራሳችን ተገፋፍተን የምናደርገው ማንኛውም ነገር መዘዙ የከፋ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ጥሪው ከመለኮት የመጣ ካልሆነ በምንሠራው ሥራ ብርታት፣ ኃይል፣ ሰላምም ሆነ በረከት አናገኝም፡፡ የእግዚአብሔርን ድምጽ የምንሰማበትና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከቃሉ አዲስ ብርታት የምናገኝበት--ከእርሱ ጋር የሚኖረን ምርጥ ጊዜ ለቅድስና ሕይወታችን በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ለሥራችን ልዩ ተዓማኒነትና አሳማኝ ኃይል ይሰጣል፡፡

*አርብ* *የካቲት 3* *........Feb 10*

## ተጨማሪ ሃሳብ

Read Ellen G. White, "Like Unto Leaven," pp. 95-102 in Christ ' s Object Lessons .

እግዚአብሔር እጅግ በአስገራሚ ቅድስና ውስጥ የሚኖር አምላክ ሆኖ ሳለ እኛ በወደቀውና በተበላሸው ተፈጥሮአችን የእርሱን ቅድስና በጥቂቱ እንኳ መልከት ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? ቅድስናው--እኛ ሰብዓዊ ፍጡራን ከተለማመድነው ከዚህ ዓለም ኃጢአትና ሞት የተነጠለና ብርቅዬ አድርጎ ያስቀምጠዋል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ አስገራሚውን ነገር የምናገኝ ሲሆን ይኸውም እግዚአብሔር የእርሱ ቅድስና ተካፋዮች ለመሆን የሚያስችለንን ዕድል ለእኛ መስጠቱ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር በተገባው ኪዳናዊ ግንኙነት እንዲህ ብሎአል "ለመላው የእስራኤል ሕዝብ ጉባዔ እንዲህ ብለህ ተናገራቸው 'እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ' " (ዘሌዋ. 19፡2)፡፡ ደግሞም የዕብራውያን መጽሐፍ እንዲህ ይለናል "ከእስራኤል ቤት ጋር፣ ከይሁዳም ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል፤ ይላል ጌታ፡፡... ከዚያን ጊዜ በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው፤ ይላል ጌታ፤ ሕጌን በአእምሮአቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፡፡ እኔ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ፡፡"(ዕብ. 8፡8, 10)፡፡ በቅድስና፣ በኪዳንና በሕጉ መካከል በጥቅሶቹ ትስስር መኖሩን መመልከት እንችላለን፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ ሳንታዘዝ ቅዱስ መሆን ስለማንችል፤ የእርሱን ሕግ የምንታዘዘው ትእዛዛቱን በልቦቻችንና በአእምሮአችን እንደሚጽፈው እንደ ራሱ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ሕጉን በፍቅር በመታዘዝ "የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን" (ዕብ. 12፡10) የተቀደሰ ልዩ መብትና ጥቅም ተሰጥቶናል፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች:-**

- በማክሰኞ ትምህርት መጨረሻ አንድ ሰው በኃጢአት ላይ አሸናፊ ሊያደርገው የሚችለውን ተስፋ እንዴት በሕይወቱ ማግኘት እንደሚችል ለተጠየቀው ጥያቄ መልስዎን ያካፍሉ።
- የእግዚአብሔር ሕግ በልባችንና በአእምሮአችን ተጽፎአል ማለት ምን ማለት ነው? በድንጋይ ገበታ ላይ ከተጻፈው ይህ የተለየ የሆነው ለምንድን ነው?
- ስለ እግዚአብሔር ቅድስና ሲያስቡ ወደ አእምሮዎ የሚመጣው ምንድን ነው? የሰንበት ትምህርት ጥናት አባላት የእግዚአብሔርን ቅድስና እንዴት አድርገው በአእምሮአቸው እንደሳሉ ያካፍሉ። የሱስ ስለ እግዚአብሔር ቅድስና የገለጸልን ነገር ምንድን ነው?
- ለቅድስናችን መሰረቱ ምንድን ነው? የቅድስና ባለቤት መሆን የምንችለው እንዴት ነው?
- ቀደም ብለን በረቡዕ ትምህርታችን የሚከተለው ነጥብ ተጠቅሶ ነበር፦ “የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቃችን ሊያድነን አይችልም--ፈጽሞ አያድነንም። ሕጉ ወይም አስርቱ ትእዛዛት የደኅንነት መንገድ ሆነውን አያውቁም--የዳኑት የሚጓዙበት መንገድ እንጂ።” ይህ አገላለጽ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ለሚሠራ ለተቀደሱ ክርስቲያኖች ሕጉ ሊኖረው ስለሚገባ ሚና ማስተዋል እንድንችል እንዴት ሊረዳን ይችላል?